ቀሲስ አስተርአየ
nigatuasteraye@yahoo.com
Kansas City, MO, 64151



# ምንኩስና እና ኢትዮጵያ

(ክፍል ፩)

ምንኩስና በዓለም ዙሪያ ረዥም ዘመን ያለው በተለይም የሃይማኖት፥ የባሕልና የታሪክ ምንጭ የሆኑ ጥንታውያን አገሮች የሚካፈሉት ቅርስ ነው:: አገራችን ኢቶዮጵያም ከጥንታውያን አገሮች አንዷ በመሆኗ ይህን ክቡርና የተቀደሰ ቅርስ ተቀብላ፥ ከፍሬምናጦስ ዘመን እስከእኛ ዘመን ተጠቅማበታለች:: ጥንታዊት ከሚአደርጓት ቅርሶቿም አንዱ ነው:: በምሥራቁ ዓለም ያለው ምንኩስና በየደረሰበት አገር የተነሣበትን አላማና ግቡን ሳይለቅ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: ምንኩስና ምን ማለት እንደሆነ፥ የት እንደተጀመረና እንዴት እንደተስፋፋ ለመግለጽ እሞክራለሁ::

## ምንኩስና ምንድነው?

ምንኩስና ራስን ከማነኛውም ሥጋዊ ነገር አስወግዶ፥ በገዳማዊ ሕይወት በሱባዔና በጾም ለመጠመድ ወስኖ ከዓለም መለየት ነው:: የፍልስፍናው መዝገበ ቃላትም እንዲህ ይገልጸዋል:: “A discipline of life characterized by withdrawal from the world, meditation, self-abnegation and some degree of asceticism” (1) አባቶቻችንም መነኩሴ ሞቶ እንደተቀበረ ያህል ከዘመድ አዝማድ በፍጹም ልቡ ወስኖ መለየት እንደሆነ "ወይደልዎ ለጽሙድ ከመ ይትፈለጥ በኩሉ ልቡ፥ እም አበዊሁ ወአዝማዲሁ ወሰብኡ ሕዝባውያን ከመ ተፈልጠተ ምውት እምሕያዋን"(፩) "መንኮሰ ማለት፥ ሞተ ማለት ነው" ብለው ባጭር ቃል ገልጸውታል::

## የት ተጀመረ? እንዴትስ ወደ አገራችን ገባ?

ምንኩስና ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፮ ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በቡድሐ እምነት በሕንዶች ቤተ መቅደስ ተጀመረ:: ምንኩስና፥ የተፈጥሮ ስሜቶችን የሚጠልፉ ቅርጽ፥ ድምጽ፥ ማሽተት፥ መቅመስ፥ የመሳሰሉት ባሕርያት የማያናውጹት፥ እንደ አለት ደንጋይ መሠረቱ ጽኑ፥ ጠንካራና የሕይወት መገኛ ነው:: የቡድሐ ቅዱስ መጽሐፍ የምንኩስናን ጽናት እንደዚህ ይገልጸዋል:: “Just as a rock of one solid mass remains unshaken by the wind, even so, neither forms, nor sounds, nor smells, nor tastes, nor contacts of any kind, neither desired nor undesired dharma’s, can agitate such a one. Steadfast is his thought, gained is deliverance.” (2)

እንጦንስ የተባለው ግብጻዊ ቅዱስ አባት ከላይ የተጠቀሰውን የምንኩስና ባሕርይ ተመርኩዞ በ 250 ዓ/ምሕረት ወደ ክርስትና አመጣው:: እንጦንስ ብዙ ሀብትና ሎሌወች ካሉት ሐብታም ቤተ ሰብ ተወለደ:: የአስራ ስምንት አመት ወጣት በነበረት ጊዜ እናትና አባቱ ሞቱ:: የናትና አባቱ ሞት በተፈጥሮና ፈጣሪ መካከል ቆሞ እንዲያስብ አደረገው:: የእናትና አባቱ ሞት ትተውት ከሄዱት ንብረት ጋራ እየተጋጨ "የሰው ሕይወት በዚህ የሚቆም ከሆነ የሐብት ብዛት ምን ይጠቅማል" በሚል ጥያቄ አዕምሮውን አስጨነቀው:: በአዕምሮው ውስጥ ለተፈጠረበት ጥያቄ መልስ ለማግኘት ከራሱ ጋር በሚታገልበት ወቅት፥ ከእለታት አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ:: እንዳጋጣሚ ስለሐብታሙ ሰው የሚተርከውን ሲነበብ ሰማ:: ሐብታሙ ሰውም "የዘላለም ሕይወት አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ" ብሎ ክርስቶስን እንደጠየቀና፥ ክርስቶስም "ፍጹም ልትሆን ከወደድክ ያለሕን ሽጠህ ተከተለኝ በሰማይ መዝገብ ታገኛለህ"(፪) ብሎ የሰጠው መልስ ነበር:: "Anthony was pondering his future when in church one day he heard the words Jesus spoke to rich young man: “Go, sell what, and give to the poor and you shall have treasure in heaven; come and follow me.” (3)

እንጦንስ ይህን ከሰማ በኋላ፥ አንዲት እኅት ነበረችው ድርሻዋን ሰጥቶ፥ የራሱን ድርሻ ሽጦ፥ ለድሐ መጽውቶ፥ ይህን ዓለም ንቆ (መንኖ) በመመንኮስ ወደ በርሐ ገባ:: ታሪኩ እንደሚለው አንጦንስ ይህን ያደረገው እንደአካባቢው ባሕል በአሸከር ተከቦ፥ በሐብቱ ተንደላቆ፥ በሕዝቡ ተከብሮ፥ መኖሩን ሳያውቅበት: ወይም ሳይገባው ቀርቶ አልነበረም:: ከሞት ባሻገር ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዳለ ለመረዳትና ፈጣሪውን ለመፈለግ፥ እንዲሁም ነፍሱን ለማዳን ቆርጦ በመወሰኑ ነበር:: "Anthony was not seeking an easy escape from difficulty. Instead, he abruptly abandoned a tradition and respectable life to make his own way to self-discovery-and the discovery of God. Anthony devoted himself to ascesis, which literally means “exercise”-in order to attend to his soul.” (4) ከሱም በኋላ ጳኩሚስ የተባለው ቅዱስ መነኩሴ በ 290 ዓ/ምሕረት እንጦንስ የጀመረውን ምንኩስና በሕግና በስርአት

ቀረጸው:: በ፬ ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፍሬምናጦስ በኩል ኢትዮጵያ ገባ:: ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፭ኛው ክፍል ዘመን በተሳቱ(፱) ቅዱሳን ኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፋ::

## ቡድሐና የክርስትና ምንኩስና ልዩነት

በቡድሐ ሃይማኖት፥ ቡድሐ፡ ተርካያ እና ቨስቲያን በሶስትነት ይታወቃሉ:: ቡድሐ ሶስት አይነት የመገለጫወች አካላት አሉት:: ቅዱስ የመገለጫ አካል፥ ልዩ ቅዱስ አካልና ከፍተኛ ረቂቅ አካል ናቸው:: ከነዚህ የመጀመሪያው አንዱ አካል እውነተኛውና ሪካዊው ቡድሐ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ መካከለኛ እውነት ነው:: እሱም በቁስ አካላዊው ዓለም የመጨረሻው እውነት ነው:: በሰአትና ቦታ ሁሉ በማዳን እቅድ ውስጥ በረቀቀ እቅዱ እየሰራ የሰውን ባሕሪይ የሚካፈል ነው:: ሶስተኛው ደግሞ ከቁስ አከላዊ ዓለም የራቀ የመጨረሻው እውነት የቡድሐ ሁለንተናዊ አካል ነው:: ከዋነኛው እግዝአብሔር ጋራ የሚመሳሰል ነው:: እሱም በውስጣችን ያለው የማይሞት ሕያው ነው:: ብሎ የቡድሐ ቅዱስ መጽሐፍም እንዲህ ይገልጸዋል:: "in Mahayana Buddhism; and a marked similarity is to be noticed between the Buddhist Trikaya and the Vhrstian Trinity. Buddha is to be understood as having three manifestations; as the body of Transformation; the Body of Bliss, and that of Dharma. The first of these is, roughly speaking, the historical Buddha. The second would seem to be an intermediate reality, sharing in the qualities of the physical world and of ultimate reality, while mysteriously working out schemes of salvation in all times and places The third is similar to the conception of the Godhead, the Dharmakaya which is at once the ultimate reality, and the cosmic body of Buddha, yet beyond the physical. It is the immortal in us, in Guatana Buddh, and in all other Buddhas."(5)

የክርስትናው ምንኩስና ግን የሚከተለው ክርስቶስ፥ በአብ በወልድና፥ በመንፍ ቅዱስ ስም እያስተማራችሁ አጥምቁ "እንዘ ታጠምቅወሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመን ፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ" ፫ ብሎ ያስተማረውን መሠረት ያደርጋል:: ይህን መነሻ በማድረግ ሊቃውንቱ ሁሉ ሶስቱ በባሕርየ መለኮት አንድ ናቸው፥ ከነሱ አንዱ አብ በተለየ አካሉ ከነሱ አንዱ ነው:: ወልድም በተለየ አካሉ ከነሱ አንዱ ነው:: መንፈስ ቅዱስም በተለየ አካሉ ከነሱ አንዱ ነው:: "ኢትአምሩኑ ከመ ስሉስ ቅዱስ ፩ዱ በሕላዌ መለኮት፡ ወኢይትማሰል በብዙኃን:: ወበ ከመ አብ አሐዱ፥ ወወልድኒ ፩ዱ ከማሁ፡ ወመንፈስ ቅዱስሂ ፩ዱ ውእቱ"፬ እያሉ አስተማሩ:: ሲብራሩትም "አብ ወላዲ፥ ወልድ ተወላዲ፥ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ብለውታል:: ክርስትና ሰው የሚድንበትን ሲገልጽ፥ ከሶስቱ አንዱ ወልድ ሙሉ ሰውነትን ከእመቤታችን ወስዶ በለበሰው ሰባዊ አካል አማካይነት ሰውን አዳነ:: እሱም እውነት፥ መንገድና ሕይወት ነው ይላል:: ሶስተኛው አካል መንፈስ ቅዱስ ነው:: እሱም ሰውን እውነት፥ መንገድና ሕይወት ወደ ሆነው ክርስቶስ ይመራል:: በዚህ ያመነ ሁሉ አንድ ጊዜ የሥጋ ሞት ይሞታል:: እንደገና ተነስቶ የሰውን ሥጋ ከለበሰው ከሶስቱ አንዱ ከሆነው ከክርስቶስ ጋራ ለዘላለም ነግሶ ይኖራል ብሎ ያስተምራል::

የቡድሐ ምንኩስና ደግሞ በተቃራኒው፥ ሰው የሚድንበትን እንዲህ ብሎ ይገልጸዋል:: ማነኛውም ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ እየተመላለሰ በመምጣት በሚአደርገው እድገቱ፥ የመጨረሻውን ሞት ሲሞት በመነኮሳት ሠራዊት ተከቦ ይቆማል:: "If any beings, Ananda, again and again reverently attend to this Tathagata, if they raised their hearts to enlightenment, and if they vow to be reborn in that world system, then, when the hour of their death approaches, that Tathagata Amitabha, are the fully Enlightened One, will stand before them, surrounded by hosts of monks" (6)

የቆየው ባሕል እንደመዘገበው በሕይወት ዘመን ከቡድሐ ጋራ ስምንት አይነት እድገቶች አሉ ይልና ቅዱሳን እየተመለመሉ ወደ ምንኩስናው ቡድን ይገባሉ:: የየራሳቸውን ገጽ የሚአንጸባርቅ ክታብ ይጎናጸፋሉ:: የቅዱሳንን ቅሬት ይሸለማሉ ይላል:: "Tradition lists eight arahnts associated with Buddha during his lifetime. As in the case of saints, candidates for archatahip are put forward from the company of holy monks; protective amulets bearing their images are worn: relics are prized."(7)

በእንጦንስ የተጀመረው የህርስትናው ምንኩስና ግን፥ ማንም ሰው አሕዛብ ከሚአደርጉት ከሐሰት ከስርቆት ከዝሙት ኑሮ ርቆ፥ ሥጋዊ ምኞቱን አሸንፎ፥ በሕገ ተፈጥሮ አግብቶ፥ ዘር አትርፎ፥ በንስሐና በቁርባን ተወስኖ እንደ ሐዋርያት ክርስቶስን የሚከተል ሁሉ ይድናል፡ ይላል :: "ተላውያኒሁ ለክርስቶስ በከመ ክሂሎቶሙ ወበኩሉ ምግባራቲሆሙ ተመሳልያን በሐዋርያቲሁ  በተግሕሦ እምፍጥረታተ ዓለም ወኀዲገ ፍትወታቲሆሙ፡ ወመንኖ ኩሉ ግብረ ነፍሳቲሆሙ" (፭)

አባ ሕርያቆስ የተባለው መነኩሴም፥ በትዳር የነበሩትን ሰማእታትን፥ ነብያትን፥ ሐዋርያትን ሁሉ ደርድሮ መነኮሳቱም እንዳሉበት ጠቀሰ:: "ያብእከሙ ማኀበረ ነብያት ቅዱሳን. . . .ወማኀበረ ደናግል ወመነኮሳት ፍጹማን"(፮) ይህም ማለት:- በጋብቻ ውስጥ ያለውም ሆነ በምንኩስና ያለውም፥ ሁሉም ክርስቶስን መሠረት በማድረግ በተሰለፈበት ጸንቶ ከቆመ

*መንግስተ ሰማያትን እኩል የሚወርሳት መሆኑን ለማስረዳት ያህል መነኮሳትንም ጠቀሰ:: እንደ ቡድሐው ሃይማኖት ስርአት ምንኩስናን ከጋብቻ ይልቅ ወደ ላይ እያጓነ አያሰብክም:: በዓለም መጨረሻም በመነኮሳት በተሞላች ከተማ ትገባላችሁ ብሎ አያስተምርም:: ይልቁንም ክርስቶስ በትዳር የነበሩትን "የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ" (፯) እያለ በመጥቀሱ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ክርስትና "ውስተ ሕጽነ አብርሃም፥ ይስሐቅ ወያዕቆብ"(፰) በትዳር የነበሩትን አብርሃምን ይስሐቅንና ያዕቆብን እየጠቀሰ እነሱ ባሉበት ከተማ ክርስቶስ ንጉሣችን ሆኖ እንኖራልን እያለ ያስተምራል::*

*በሉቃስ ወንጌል ተጽፎ እንደምናነበው መጋቢ ስለሚባለው የሐብታሙ ንብረት ጠባቂ በሚተረከው ላይ፥ በሕገ ተፈጥሮ ተወስነው ዘር ተክተው ንስሐ ገብተው ቆርበው የሚኖሩ ሰወች በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ያወቁበት እነሱ ናቸው ብለው ሊቃውንት አበው ተርጉመውታል:: "እስመ ውሉደ ዝ ዓለም ይጠበቡ በዓለሞሙ'(፰) በኦርቶዶክሱ ነገረ መለኮት ትምህርታችን መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፥ ትዳር ውስጥ መግባት የልብ መከፈል ስለሚያስከትል ባንድ ልብ ሆኖ ፍጥረቱን ለመመርመር ፋታ ባይሰጥም፥ ከምንኩስናው ይልቅ ፈጣሪ በሰው ላይ የጫነው ቀንበር ጋብቻ ነው:: "ወአንሰ እፈቅድ ለክሙ ዘእንበለ ሐዘን ተሀልው:: እስመ ዘኢያውሰበ ይሔልዮ ለእግዚአብሔር በዘያሠምሮ:: ወዘአውሰበ ይሄሊ ንብረተ ዝንቱ ዓለም በዘያሰምራ ለብእሲቱ:: ወበእንተ አውስቦቱ ተናፈቀ" (፲) ምንኩስና የፈለገ ሰው በራሱ ፈቃድ የሚቀበለው እንጅ የተፈጥሮ ግዴታ አይደለም::"ምንኩስናሰ እምፈቃድ ይእቲ ወአኮ በግብር" (፲፩) ምንኩስና አምላክ ከፈጠረው ከተቀደሰው ጋብቻ በላይ ቅዱስ አይደለም::*

*የኦሪቱ ሊቃውንት ስለ ጋብቻ መፍረስ አውስተው ከክርስቶስ ጋራ በተነጋገሩበት ጊዜ፥ "መሴ ባል ሚስቱን የሚፈታት ከሆነ የሚፈታበትን ምክንያት ይጻፍላት" ያለውን ጠቅሰው፥ የፍችን ተገቢነት በሚደግፍ መንፈስ ጠየቁት:: ሙሴ የፈቀደው የሰውን ደካማ ባሕርይ ለማስተናገድ ሲል እንጅ የተፈጥሮ ሕግ አይደለም ብሎ የወንድና የሴትን መለያየት በመቃወም፥ ወደ ተፈጥሮ ሕግ አመለከተ:: (፲፪ ይህም "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" የሚለው የማይሻር ቃሉ ነበር:: (፲፫)*

*ክርስቶስ ከጋብቻ ርቆ መኖርን የሚአስከትሉትን ነገሮች ከገለጸ በኋላ፥ የተፈጥሮ ሰባዊ ባሕርይው የማያውከው ሆኖ ሊፈጽመው የሚችል ካለ ያድርገው፥ "ወዘሰ ይክል ፈጽሞ ለይፈጽም" ፲፬ በማለቱ ክርስትና ምንኩስናን ያከብራል እንጅ አይቃወምም:: ይሁን እንጅ ምንኩስና ከጋብቻ በላይ ቅዱስ ነው ብሎ አያስተምርም:: ጋብቻና ምንኩስና ወድድር ውስጥ የሚገቡ ከሆነ ከምንኩስና ይልቅ በጋብቻ ተወስኖ መኖሩ እንደሚበልጥ የክርስትና መጻሕፍቶቻችን ይመሰክራሉ::*

*አምላክ በጥበቡ ዘር ማመንጨት እንድንችል ቀምሞ ፈጠረን:: ይህም ወደዚህ ዓለም ስንመጣ ከምን ፈጽማቸው ግዴታወቻችን አንዱ በመሆኑ በጋብቻ ተወስነን ዘር ተክተን ለማለፍ የምንጎናጸፈው ጸጋ ነው:: በድንግልና ሕይወታቸውን ያሳለፉት መምህሮቻችን ሊቃውንቱም፥ ድንግልናቸውን ለቅዱስ ጋብቻ ዝቅ አርገው፥ ለጋብቻ ያላቸውን አክብሮት አረጋግጠው አስተምረውናል:: በትዳር ተወስነው በቁርባንና በንስሐ ውስጥ ሆነው ዘር አትርፈው ሕይወታቸውን በመምራት ያሉትንም ከነሱ ይልቅ ቅዱሳን ኃያልን እንደሆኑ በጉባዔያቸው እያረጋገጡ አስረድተውናል:: አንድ ሰው የተፈጥሮ ችግር ካልገጠመው፥ ወይም ከፈጣሪው የተለየ ጥሪ ካልደረሰው በስተቀር፥ ኑሮን ለመወጣት የሚገጡሙትን እንደ ድሕነት ያሉ እንቅፋቶችን ባቋራጭ ለማምለጥ መመንኮስ በሥጋም ሆነ በነፍስ መቃጠልን ያተርፋል እንጅ አያጸድቅም ይላሉ:: መጽሐፍም "ብዙ ተባዙ ምድርን ምሏት"(፲፭) ብሏል:: "ይህም ማለት ምንኩስና የግል፥ ጋብቻ ግን ሕግ መሆኑን ያመለክታል" ይላሉ::*

## የቡድሐና የክርስትና ምንኩስና ተመሳሳይነት

*የቡድሀውና የክርስትናው ምንኩስና በዓለም ውስጥ ከሚደረገው ሥጋዊ ነገር መሸሽ፥ በዓለም እያሉ እራስን ከዓለም እንደሌሉ አርጎ መቁጠር ::* "self abnegation or self dinaial " *በሚለው ያኗኗር ስርአት ተመሳሳይ ናቸው:: የቡዳሐ ስርአተ ምንኩስና፥ ምንኩስና ከዝቅተኛ ምግባረ ሠናይ ተነስቶ ከከፍተኛ ጥልቅ መንፈሳዊነትና ጥበብ ላይ የሚደርስ ነው::* "The monks alone can hope to advance from morality to higher things, first to meditation, and then to wisdom"(8) *ብሎታል:: የምንኩስና ተግባሩ ይህ ብቻ እንዳልሆነም:: በሌላ ቦታ አጠንክሮ ሲአብራራ፥ የሚታማበት እንከን የሌለው የተቀደሰ ሕይወት ለማነኛውም ግብ መሠረት ቢሆንም፥ ለምንኩስና ሕይወት ግን ከዚያ የበለጠ ነው::* "A morally blameless or virtuous life is the basis of all other achievements "(9) *ብሏል:: የቡድሐውና የክርስትናው ምንኩስና በርእዮተ-መንፈሳቸውና ዓለማቸው ቢለያዩም፥ ከቁስ አካላዊ ዓለም ጋራ ያላቸውን ግንኙነት ቆርጦ በመጣል፥ ምድራዊ ሕይወትን የመንፈስ ልዕልናና የሕሊና ጽዳት፥ ምንጭ በማድረግ ይስማማሉ:: የሚኖሩባቸውን ገዳማት የሞራል የመንፈስና የስነ ጽሑፍ ደሴቶች አድርገዋቸዋል:: ዓለማችንን የስነ ጽሑፍ፥ የታሪክ፥ የትምህርትና የስነ ምግባር ባለቤት በማድረጋቸውም ይመሳሰላሉ::*

*መነኩሴ በገዳም ከሚኖሩት ጓዶቹ ጋራ አንድ አካል ስለሆነ ከማኅበሩ ተለይቶ አንዳች ነገር ማድረግ*

የለበትም:: ክርስትና የባልና ሚስትን ተፋቶ መለያየት ሞት ነው እንዳለው ሁሉ መነኩሴም ከገዳሙ ከተለየ የሞተ ነው:: "ወአልቦቱ ለ፩ዱ እምኔሆሙ ሥልጣን ላዕለ ምንትኒ ይግበር እምኔሁ ግብረ ለዓለማውያን ወኢለቅሩባኒሁ ሥጋውያን ወኢለርእሱ አላ ለአኀዊሁ መነኮሳት ዘኮነ ፩ዱ ያታ: ወለ እልክቱኒ አልቦሙ ሥልጣን ላዕለ ርእሶሙ ከመ ይትፈለጡ እማእሰረ ተአኀዋት መንፈሳዊት: በከመ ኢይትከሐል ተፈልጦተ ተዋስቦ ዘእንበለ ሞት"፲፮ ይለዋል::

የክርስትና መነኩሴ ከዓለም ለመለየት በሥጋው ላይ ሞት ያወጀበትን ቃል ኪዳን በመወላወል አፍርሶ መንፈሳዊ ሕይወቱ እንዳይቃወስ ከገዳም መለየት የለበትም:: "ይደልዎ መቅድመ ኩሉ ግብር ለዘይመጽዕ ኀበ ዛቲ ትሩፋት: ከመ ይኩን ሎቱ ሕሊና ጽኑዕ ዘኢያንቀለቅል ለፈጽሞ ኪዳን ዘተካየዶ ወኢይግባእ ኀበ ድኅር ወከመ ይፈጽም ትእዛዞሙ ለሊቃውንት ዘላዕሌሁ ወይሕሥስ ዘይደሉ ለመድኀኒተ ነፍሱ" (፲፯) ይላል:: የቡድሐ መነኩስና ስርአት፥ መነኩሴ በምግብ ሆዱን ከሞላ የማስተዋሉን ኃይል ያጣል:: መንፈሱ ለውጩ ዓለም ይጋለጣል:: በመንፈስ ልዕልና ፈጽሞ አያድግም:: እውቀትና ጥበብም ሊኖረው አይችልም "When a monk is full of himself, is heedless and given to things that are outside, he can never make progress in moral perfection, in trance or in wisdom"(10 ) ይላል:: ጭንቀትህ ፍላጎትህ ስሜትህ እወርሳታለሁ ብለህ ስለምትመኛት መንግሥተ ሰማያት ብቻ ይሁን "ወኢይኩን ለከ እንከ መባሕት ወኢምንትኒ እምዘሀሎ ውስተ ዝንቱ ዓለም:: አላ ጸሐቅ ለመድኃኒተ ነፍስከ:: ወፍትወትከኒ ይኩን ውስተ መንግሥተ ሰማያት ዘአንተ ትሴፈዋ ወተአምን ዘከመ ትረክባ"(፲፰) በሚለው የቡድሐውና የክርስትናው ምንኩስና ይስማማሉ::

ባጠቃላይ ምንኩስና ከቡድሐ ሥርአተ ሃይማኖት መንጭቶ፥ ክርስትና ውስጥ ሰርጾ ወደ አገራችን የገባ የቅድስና ኑሮ ነው:: ምንኩስና በጾም በጸሎት ተጠምዶ፥ ዓለምን ንቆ በገዳማት የመኖር ስርአትን የሚገልጽ ቃል ነው:: ይህንን መሠረት በማድረግ በተከታታይ ለማቀርባቸው ጽሑፎች የእግዚአብሔር ረድኤትና የፍጹማን መነኮሳት በረከት እንዳይለየኝ እመኛለሁ::

ይቆየን


English references

1.William L. Reese (Dictionary of Philosophy, page 491) US, 1999
2. Edward Conze, (Buddhist Scriptures page 183) England, 1959
3. Elaine Pagels, (Adam and Eve, page 82) New york, 1943
4. Elaine Pagels, (Adam and Eve, page 82) New york, 1943
5. Edward Conze, (Adam and Eve, page 96) New york, 1943,
6. Edward Conze, (Adam and Eve, page 97) New york, 1943,
7. Edward Conze, (Buddhist Scriptures, page 23) England, 1943
8. Edward Conze, (Buddhist Scriptures, page 70) England, 1943 ,
9. Edward Conze, (Buddhist Scriptures, page 69) England, 1943
10.Edward Conze, (Buddhist Scriptures page 85) England, 1959

ግእዝ ተጠቃሽ ማስረጃ

፩ ፍ.ነገ አንቀጽ ፲:፫፹፭
፪ ማቴ ፲፱:፲፮-፳፪
፫ ማቴ ፳፰:፲፱
፬ ሃ.አበው ፴፫:፲፱
፭ ፍት.ነገ አን ፲:፫፻፴፬
፮ ቅ. ማር ገጽ ፻፹፯:፻፶፱
፯ ማቴ ፳፪:፴፪
፰ ቅ. ፻፪:፹፭
፱ ሉቃስ ፲፮:፰
፲ ፩ኛ ቆሮ፯:፴፰
፲፩ ፍት.ነ አ. ፲:፫፶
፲፪ ማቴ ፲፱:፭-፰
፲፫ ዘፍ ፪:፲፰
፲፬ ማቴ ፲፱:፲፪
፲፭ ዘፍ ፩:፳፰
፲፮ ፍ ነ አን ፲:፫፻፹፰
፲፯ ፍ ነ አን ፲: ፫፻፵፮
፲፰ ሃ ምዕ ፳፩:፳፰